# እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!

**<u>በቤተ ክርቲያን የተዘጋጀ ታላቅ ሪትሪት</u>**

ቀን፡ **7/4 - 7/6/2019**
**አድራሻ፡** W2511 WI-23, Green Lake, WI 54941 (Takes about 3 hours to 3:30 hours)
**Phone** = (920) 294-3323 Booking ID number= 14589
For making reservation please call during the below hours
**Sunday - Thursday 8:30-4:30**
**Friday - Saturday 24 hours**
**When reserving rooms please provide the date, the name Yemsrach how many people will be in the room.**

## የአርብ ፕሮግራም

በአርብ ፕሮግራም እግዚአብሔር ግሩም የጸሎትና የትምህርት ጊዜ እየሰጠን ነው። በዚህ የጸሎት ፕሮግራም ላይ በመገኘት በጸሎትና ቃሉን በመማር እንድንተጋ ቤተ ክርስቲያን ታሳስባለች። እንዲጸለይላችሁ የምትፈልጉ ወገኖችም መሪዎችን ማነጋገር ትችላላችሁ። ጌታ ይባርካችሁ።

## የእሁድ 1:30 ጸሎት

እሁድ ልክ 1:30 ላይ ተገናኝተን በጸሎት እንድንተጋ ቤተ ክትርስትያን አጥብቃ ታሳስባለች። በተከታታይ በዚህ ሰአት በእግዚአብሔር ፊት የምንጸልይባቸው ጉዳዮች ስላሉን ልክ በሰዓቱ እንድንገኝ እናሳስባለን።



- ⇒ **የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?**
- ⇒ **የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?**
- ⇒ **በምጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?**
- ⇒ **ማገልገል ይፈልጋሉ?**
- ⇒ **Yeec.org App ጭነዋል?**
- ⇒ **http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?**

**ሽማግሌዎችን ለማግኘት፡-**
**773-886-0818 (ወ/ም ሲሳይ)**
**773-507-0147 (ወ/ም ጸደቀ)**
**630-677-0293 (ዶ/ር ተረፈ)**
**773-910-0486 (እ/ት ሰናይት)**
**773-556-5345 (ወ/ም ረድኤቱ)**

**<u>መደበኛ ፕሮግራሞች</u>**
እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.
አርብ 7:00 p.m. -- 9:00 p.m.

| የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን | | Chicago Yemsrach Evangelical Church |
|---|---|---|

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2:10



"እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል፥ ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል::"
(ያዕ. 4:6)

Chicago Yemsrach Evangelical Church
4455 N. Seeley Avenue
Chicago, IL 60625

መደበኛ ፕሮግራሞች
እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.

**March 24, 2019** | **መጋቢት 15፣ 2011 ዓ.ም.**

# የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

ጸሎት ................. ወ/ም ጌቱ ጳውሎስ

አምልኮ...................... የቤት ክርስቲያን የአምልኮ ቡድን

ፕሮግራም መሪ .......... ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ

ቃል ............. ፓ/ር ሞር (Pastor Moore)

ማጠቃለያ ................. ፕሮግራም መሪ

## <u>የሳምንቱ ጥቅስ</u>

“ነገር ግን ወደዚህ ወደ ትሑት፥ መንፈሱም ወደ ተሰበረ፥ በቃሌም ወደሚንቀጠቀጥ ሰው እመለከታለሁ።” (ኢሳ. 66:2)

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች**

| መሪ | ቀን | አድራሻ |
|---|---|---|
| ወ/ም አያሌው አሰፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሃሙስ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| | | |

# መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

## ከሁሉም የሚበልጠው ማንነት!

*“ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፥ ሁሉም አዲስ ሆኖአል።” (2ቆሮ 5:17)*

ከጥቂት ጊዜ በፊት አልፍሬድ ፖስቴል ስለሚባል አንድ ሰው አነበብኩኝ። ሚስተር ፖስቴል አሁን ቤት-የለሽ (homeless) እና የአእምሮ እምምተኛ ነው። ሚስተር ፖስቴል በጣም የተማረና ትልቅ ስራ የነበረው ሰው ነው። ከታዋቂው የሃርቫርድ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ዲግሪ ተቀብሏል። እንዲሁም የኢኮኖሚክስና የአካውንቲንግ ዲግሪዎች አሉት። በጣም ታዋቂ ከሆኑ ሰዎች ጋር (የአሁኑን የአሜሪካን ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰብሳቢ ዳኛ ጨምሮ) አብሮ የመማር እድል ነበረው። በጊዜውም ትልቅ ደሞዝ እየተከፈለው ለታወቀ የሕግ ድርጅት ይሰራ ነበር። ነገር ግን በሕይወቱ በገጠመው ሳንካ የተነሳ አሁን በኑሮ የመጨረሻ ጠርዝ ላይ ይገኛል።

የሚስተር ፓስቴልን ህይወት ያነበበ ሁሉ ስለ ማንነቱና ስለ ህይወቱ ትርጉም ማሰቡ አይቀርም። ማንነታችንን ባለን የትምህርት ደረጃ፣ ስራ፣ የገንዘብ ሃብት፣ ማህበራዊ ስፍራ አንጻር የምንመዝን ከሆነ አስተማማኝ መሰረት ላይ አልቆምንም። እንኚህ ሁሉ በቀላሉ የሚሸረሸሩና የሚያልፉ ነገሮች ናቸው። ነገር ግን እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ ከዘር፣ ከቋንቋ፣ ከትምህርት ደረጃ፣ ከሃብት፣ ከማህበራዊ ስፍራ ... ወዘተ ያለፈ ማንነት ሰጥቶናል። ቃሉ “አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፥ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም፥ ወንድም ሴትም የለም፤ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁ” (ገላ. 3፡28) ይለናል። እንዲሁም ቃሉ የሚመካ በእግዚአብሔር ይመካ እንደሚል፤ ትምክህት ካስፈለገ የምንመካበት ማንነት በክርስቶስ ኢየሱስ ያገኘነው ማንነት ነው። ይህ ማንነት ነው ምድራዊውን ተሻግሮ ለሰማያዊ ርስት የሚያበቃን። ይህ ማንነት ነው በምድርም ስንኖር የማያቋርጥ የሰላም ምንጭ የሚሆነን። ለዚህ ነው ቃሉ በሌላ በምንም ሳይሆን በጌታ ደስ ይበላችሁ የሚለን። በሌሎችን ነገሮች ለጥቂት ጊዜ ደስ መሰኘት ይቻል ይሆናል። ዘላቂ የውስጥ ሃሴት የሚገኘው ግን በጌታ ላይ ባለን ማንነት ብቻ ነው።

ይህንን ጉዳይ በጥልቀት የተረዱ የእምነት አባቶች ምድራዊውን ነገር ንቀው በተፈጠሩበት ዘላቂ ማንነት ኖሩ። ለዚህ መቼም ከሐዋሪያው ቅዱስ ጳውሎስ የሚበልጥ አብነት የለንም። እርሱ በምድር ባሉ የክብር መለኪያዎች ተወዳዳሪ አልነበረውም። በትውልድ የቢንያም ወገን ነው፣ እብራዊ ነው፣ ፈሪሳዊ ነው፣ ከገማልያል እግር ስር ቁጭ ብሎ የተማረ የሕግ አዋቂ ነው። ነገር ግን ይህንን ሁሉ ክርስቶስን ከማወቅ ጋር ሲያነጻጽረው እንደ ጉዳትና እንደ ጉድፍ እቆጥረዋለሁ ይላል። (“አዎን፥ በእውነት ከሁሉ ይልቅ ስለሚበልጥ ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ ስለ ጌታዬ እውቀት ነገር ሁሉ ጉዳት እንዲሆን እቈጥራለሁ፤ ስለ እርሱ ሁሉን ተጐዳሁ፥ ክርስቶስንም አገኝ ዘንድ፥ በክርስቶስም በማመን ያለው ጽድቅ ማለት በእምነት ከእግዚአብሔር ዘንድ ያለው ጽድቅ እንጂ ከሕግ ለእኔ ያለው ጽድቅ ሳይሆንልኝ፥ በእርሱ እገኝ ዘንድ ሁሉን እንደ ጉድፍ እቈጥራለሁ” ፊሊ. 3፡ 8-9)። የእምነት አባት ሙሴም ስለሚበልጠው በክርስቶስ ስላለው ክብር የግብጽን ባለጠግነትና ክብር እንቢ ብሎ ከወገኖቹ ጋር መከራ መቀበልን መረጠ። ለምን ቢሉ በአለም (“በግብጽ”) ካለው ማንነት ይልቅ በክርስቶ ያለው ማንነት እጅግ የከበረና የበለጠ እንደሆነ ስለተረዳ ነው። ወገኖቼ፡- የሚስተር ፓስቴልን ሕይወት ስናንብ በእርግጥም በዓለም ያለ ማንነትና ክብር በቅጽበት የሚለወጥና የሚጠፋ ነው፤ ምድራዊና ጊዚያዊም ነው። የሚጸናው በክርስቶስ ያገኘነው ማንነት ነውና በዚያ እንኑር!